ከእንግዳ፡ታደሰ

# ደሞ፡ የምን፡ ማልቀስ!!



ደሞ፡የምን፡ማልቀስ፣
ያልፈጠረበትን፡ቴዎድሮስ፣
ከገጸ፡ፊቱ፡እምባ፡ማበስ፣
ኮስተር፡ሲል፡እንጂ፡የሚለው፡ደስ፡፡

አትስሙ፡የጠላት፡ወሬ፡ነው፣
እሱ፡ያለቀሰው፡ለፍትህ፡ነው፣
በህገ፡አራዊት፡ለታሰረው፣
ለመላ፡ጦቢያ፡ህዝብ፡ነው፡፡

አይምሮህን፡ላይሸብቡ፡አይቻላቸው፣
ለጆችህ፡ካቴና፡ቢያጠልቁላቸው
ብዕር፡ጨባጭ፡ጣቶችህን፡አያቆሟቸው፣
ይጽፋሉ፣ያፈልቃሉ፣አይከልሏቸው፣
እንደለያዩበት፡ካርታ፡አያጥሯቸው፡፡

እንደቀዳማይ፡ቴዎድሮስ፣ ለአንድነት፡መዘመርህ፣
ስላልተወደደ፣በጎጠኞች፡መልካም፡ትልምህ፣
እንደ፡ዳንቴል፡ተብትበው፡ክስ፡ቢለጥፉልህ፣
ድሀውን፡ገለው፡ባንተ፡ጭዳ፡ቢያደርጉብህ፣
ማን፡ሰምቷቸው፡የክስ፡ድሪቶ፡ቢደርቱብህ፡፡

አንድ፡ ሆነን፡አብረን፡እንኑር፡
ብለህ፡ባዜምክ፡ በፍቅር፣
አሸክሎች፡አቂመውብህ፣
ምድረ፡መንጋ፡ወያኔ፡አሲሮብህ፣
በህገ፡አራዊት፡ዘመቱብህ፡፡

አትስሙ፡የጠላት፡ወሬ፡ነው፣
እሱ፡ያለቀሰው፡ለፍትህ፡ነው፣
በህገ፡አራዊት፡የታሰረው፣
ለምየ፡ጦቢያ፡ሲል፡ነው፡፡